QuickNotes mcps

**የ2014 የትምህርት መጀመርያ (ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ) በአል አያምልጥዎት**

ቅዳሜ ኦገስት 23 ቀን 11a.m. እስከ 2 p.m. የሚካሄደው የMCPS የትምህርት መጀመርያ (ወደ ትምህርት ቤት መመለሻ) በአል እንዲያመልጠዎ አይፈልጉም፣ ቦታውም በCarver Educational Services Center፣ 850 Hungerford Drive፣ Rockville ነው። በሙዚቃ፣ በመዝናኛዎች፣ በልጆች እንቅስቃሴዎች፣ ስጦታዎችና ሌላም ሌላም እየተደሰቱ፣ የትምህርት አመት መጀመሪያ የደመቀ ክውነት እንዲገኙና ስለትም/ቤት ስርአት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች እንዲማሩ፣ ሁሉም የMCPS ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ተጋብዘዋል።

እባክዎ በበአሉ ወቅት በጀርባ የሚያዝ ቦርሳ የማይታደል መሆኑን ይወቁ፣ ነገር ግን ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች እንዲታደሉ ለትምህርት ቤቶች ይሰጣሉ። ይህን በተመለከተ ስለሚደረገው ጥረት ከMCPS Give BACKpacks ድረ ገጽ ይበልጥ ይማሩ።

በቀናት መቁጠሪያዎ ምልክት ያድርጉና አይታዎን በመቀጠል በBack-to-School Fair ድረ ገጽ ላይ የሳመር ወቅት አዳዲስ መረጃዎችን ይከታተሉ!

**በሳመር ወቅት ተማሪዎች ነጻ ምግብ ይሰጣሉ**

በበርካታ የሳመር ትምህርት ቤት ወይም የሳመር መዝናኛ ፕሮግራሞች ተማሪዎች ምግብ የሚሰጣቸው ሲሆን ይህም እንደ Montgomery County የሳመር ምግብ ፕሮግራም አካል ሆኖ የሚታይ ነው። ፕሮግራሙ የትምህርት ቀርስና ምሳ በማይሰጥበት የሳመር ወራት ወቅት ከዝቅተኛ ገቢ አካባቢ የሆኑ ተማሪዎች ገንቢ ምግብ ማግኘታቸውን እንዲቀጥሉ የሚያረጋግጥ ነው።

ነጻ ምግቡ በስራ ቀናት ከጁን 16 እስከ ኦገስት 15 (ከጁላይ 4 በስተቀር) ከ110 በሚበልጡ ጣቢያዎች በሙሉ ካውንቲው ይታደላል። እድሜያቸው 18 እና ከዚያ በታች የሆኑ ተማሪዎች፣ እንዲሁም የአካል እና የአእምሮ ጉዳተኛ የሆኑ እድሜያቸው አስከ 21 ድረስ የሆኑ ምግብ ለማግኘት ይችላሉ።

እንደ ሃይማኖት፣ ማህበረሰባዊ ተቋማት እና የመኖሪያ ቦታዎች የመሳሰሉ ሌሎች አካባቢያዊ/ማህበራዊ ቦታዎች የምግብ አገልግሎት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለ ጣቢያዎች/ቦታዎች እና ምግብ የሚያሰጡ መስፈርቶችን በተመለከተ እንደ ጉዳዩ መረጃ ለማግኘት በሚከተለው ኢሜል ይላኩ SummerFoodProgram@mcpsmd.org።

በተጨማሪም በሙሉ በካውንቲው በበርካታ ቦታዎች 18 እና ከዚያ በታች እድሜ ለሆኑ ተማሪዎች በየእለቱ በድንገት ሄደውም ምሳ ይሰጣቸዋል። ቦታዎችንና የምግብ ሰአትን በተመለከተ የተወሰነ መረጃ ለማግኘት፣ እዚህ ይጫኑ።

ለተጨማሪ መረጃ የምግብና ስነምግብ አገልግሎቶች ክፍልን (Division of Food and Nutrition Services) በ301-840-8170 ይገናኙ።

Division of Food and Nutrition Services (የምግብና የስነምግብ አገልግሎቶች ክፍል)

**የስድስት-አመት የትምህርት ቤት ግንባታ እቅድ ጸደቀ**

የMontgomery County Council የ$1.53 ቢሊዮን የስድስት-አመት የCapital Improvement Program (CIP) ለMontgomery County Public Schools (MCPS) ያጸደቀ ሲሆን ገንዘቡም በዲስትሪክቱ ለተጨናነቁት ችግር ማቃለያ የሚሆኑ አስፈላጊ ቦታዎችን ለመጨመር የሚያስችሉ በርካታ ፕሮጀክቶች የሚሆን ነው። ይሁን እንጂ የጸደቀው CIP የMontgomery County የትምህርት ቦርድ ከጠየቀው በ$214 ሚሊዮን ያነሰ እና ለበርካታ ፕሮጀክቶች መዘግየት ያሚያስከትል ነው።

የትምህርት ቦርድ ለ2015-2020 የበጀት አመታት የስድስት አመት CIP $1.74 ቢሊዮን ጠይቆ የነበረ ሲሆን ይህም በዲስትሪክቱ በፍጥነት በማደግ ላይ ያለውን ተመዝጋቢ ለማስተናገድ የሚያስችል የበርካታ አዲስ ትምህርት ቤቶች የማስፋፋት ፕሮጀክቶችን የሚያካትት ነበር። የMCPS ተመዝጋቢ ባለፉት ስድስት አመታት በ14,000 ተማሪዎች ያደገ ሲሆን በቀጣይ ስድስት አመታት በተጨማሪ በ11,000 ተማሪዎች ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል።

የቦርዱ CIP መሰረት ያደረገው MCPS ያለበትን የክፍል ውስጥ መጨናነቅ ለማቃለል እንዲሁም በዲስትሪክቱ በማርጀት ላይ ያሉ ትምህርት ቤቶችን ለማደስና ለማስፋፋት የተቀየሱ ፕሮጀክቶችን ማስፈጸሚያ ለማገዝ የሚያስችል ተጨማሪ ገቢ ከስቴቱ ህግ አውጭ ያገኛል በሚል ግምት ነበር። ይሁን እንጂ የስቴቱ ገንዘብ አልጸደቀም።

ተጨማሪ የስቴት ገንዘብ ሳያካትት፣ የካውንቲው ምክር ቤት የ$1.53 ቢሊዮን CIP አጸደቀ ይህም በ2013-2018 የበጀት አመት ከነበረው የስድስት አመት CIP በ$180 ሚሊዮን ከፍ ያለ ነው።

የጸደቀው CIP በ12 ኤሌሜንታሪ ትምህርት ቤቶች ተጨማሪ ክፍሎችን የሚያካትት ሲሆን በዲስትሪክቱ ክፍተኛ የምዝገባ እድገት የተከሰተባቸውን አምስት የDowncounty Consortium ይጨምራል። ክፍሎችን ለመጨመር ባለፈው CIP ጸድቀው የነበሩ ፕሮጀክቶች እና ከ2017 በፊት እንዲጠናቀቁ

የታቀዱት በእቅዱ መሰረት ይከናወናሉ። ይሁን እንጂ በ2017 እና ከዚያ በኋላ እንዲጠናቀቁ የታቀዱ ክፍሎችን የመጨመር ፕሮጀክቶች በአንድ አመት ይዘገያሉ።

CIP ስድስት የማደስ/የማስፋፋት ፕሮጅርክቶች-ቀደም ዘመናዊ ማድረግ የሚባለውን-በተያዘው እቅድ ለማከናወን ያስችላል፤ ነገር ግን 20 ሌሎች ፕሮጀክቶችን ያዘገያል። የእድሳት/የማስፋፋት ፕሮጀክቶች በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለአንድ አመት እና በኤሌሜንታሪ ትምህርት ቤቶች ለሁለት አመት ይዘገያሉ።

CIP በእቅድ መሰረት የሚከፈቱ ሶስት አዲስ ትምህርት ቤቶችን የሚያካትት ሲሆን ይህም በኦገስት 2014 የሚከፈተውን Wilson Wims Elementary የClarksburg ምድብን ይጨምራል። በተጨማሪም በእቅዱ መሰረት አዳዲስ መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በClarksburg/Damascus ምድብ (ኦገስት 2016) እና በBethesda-Chevy Chase ምድብ (ኦገስት 2017) ይከፈታሉ። ይሁን እንጂ አዳዲስ ኤሌሜንታሪ ትምህርት ቤቶች በRichard Montgomery እና Northwest ምድቦች በአንድ አመት የዘገዩ ሲሆን በኦገስት 2018 ለመክፈት እቅድ ተይዟል።

**አቅርቦቶችን በመኪና ለማመላስ በጎ ፈቃደኛ ተማሪዎች ይፈለጋሉ**

የመካከለኛ እና ከፍተኛ ደረጃ በጎ ፈቃደኛ ተማሪዎች ለትምህርት ቤት የተለገሱ አቅርቦቶችን ለማጓጓዝ ለተቋቋመው የአቅርቦቶች ፕሮጀክት ለመለየት፣ ለማሸግ እና ለማደራጀት ይፈለጋሉ። ይህ በቅድሚያ-የተወሰነ (የተፈቀደ) ያለበት የተማሪ የመማሪያ አገልግሎት (Student Service Learning) እንቅስቃሴ ነው። መለያየቱ የሚካሄደው በRichard Montgomery High School ካፍቴሪያ ከጁላይ 8-9 9፡30a.m. እስከ 2p.m. ነው።

አቅርቦቶች የሚገኙት ከMCPS ተማሪዎችና ሰራተኞች ሲሆን ይህም በትምህርት አመቱ መጨረሻ የእቃ ማስቀመጫቸውን፣ ጠረጴዛዎችን እና የልብስ ማስቀመጫዎችን በሚያጸዱበት ወቅት የሚያሰባስቡትን እና የሚለግሱትን አዳዲስ ወይም በጥንቃቄ የተጠቀሙበትን የትምህርት ቤት መገልገያ ይመለከታል።

አቅርቦቶችን በመኪና ለማመላለስ ማሰራጨቱ ሰኞ ጁላይ 14፣ Richard Montgomery High School ካፍቴርያ፣ 250 Richard Montgomery Drive፣ በRockville ይካሄዳል። ከህዝባዊው ውይይት በኋላ ወዲያውኑ በጎ አድራጎት ተቋማትና ቤተሰቦች አቅርቦቶችን መውሰድ ይችላሉ። ቅድመ-ምዝገባ ለበጎ አድራጎትና ትምህርት ቤቶች አስፈላጊ ነው።

አቅርቦቶችን በመኪና ማመላለስ

QuickNotes mcps

## "Fizz-Boom-READ!" በዚህ ሳመር በእርስዎ የህዝብ ቤተ መጽሀፍ

Montgomery County Public Libraries (MCPS) (የሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ቤተ መጽሀፍት) ከጁን 1 እስከ ኦገስት 31 በሚካሄደው የዚህ አመት የሳመር ንባብ ፕሮግራም እንዲሳተፉ ሁሉንም ተማሪዎች ይጋብዛል።

ተሳታፊዎች ለፕሮግራሙ መመዝገብና ያነበቧቸውን ወይም የተነበቡላቸውን መጻህፍት ዝርዝር ማዘጋጀት ይችላሉ። ምዝገባ በቀጥታ በኮምፒውተር መስመር እና በማንኛውም የMCPL ቅርንጫፍ ቤተ መጽሀፍ ማካሄድ ይቻላል። ፕሮግራሙ ሲጠናቀቅ ሽልማቶች (አቅርቦቶች እስኪያልቁ ድረስ) ይሰጣሉ።

ሳመሩን በሙሉ ምታት፣ ሳይንስ፡ እንስሳት፣ ምስሎች፣ ተረቶችን መንገር እና ሙዚቃን የሚያካትቱ ነጻ ፕሮግራሞች ይኖራሉ።

## Fall Athletic Tryouts (የፎል አትሊቲክ ሙከራ) ልምምድ ኦገስት 13 ይጀምራል።

የአትሌቲክ ሙከራና ልምምድ በብዙ MCPS 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የፎል ስፖርት ቡድኖች እሮብ ኦገስት 13 ይጀምራል። የፎል ስፖርት ፉትቦል፣ የሜዳ ሆኪ፣ የወንዶችና ሴቶች ልጆች እግር ኳስ፣ የሴቶች ልጆች መረብ ኳስ፣ የሴቶች ልጆች ቴኒስ፣ ትምህርታዊ አገር አቋራጭ፣ ትምህርታዊ የጎልፍና የቀጣይ ቡድን እጅ ኳስ ያካትታል። ተማሪዎች የሚፈልጉትን የልምምድ ቀን፣ ሰአት እና ቦታ ለመወሰን የትምህርት ቤታቸውን አትሌቲክ ሃላፊ ማማከር ወይም የትምህርት ቤታቸውን ድረ-ገጽ መጎብኘት አለባቸው። ተማሪዎች በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አትሌቲክስ ለመጫወት አመታዊ አካል ምርመራ ሊኖራቸው ይገባል።

በአንድ ቡድን ከመሳተፍ አስቀድሞ በተማሪ፣ ወላጅ እና ዶክተር ወይም ነርስ ፕራክቲሽነር የተፈረመ የጤና ቅጽ፣ የተሞላ የድንገተኛ ወቅት የህክምና መዝገብ፣ እና የተማሪ-ወላጅ ስምምነት/ፈቃደኛነት ቅጽ መሰጠት አለበት። ተጨማሪ ቅጾች ሊያስፈልግ ይችላል። ቅጾችን በሚመለከት የአካባቢዎን የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይገናኙ።

አትሌቲክስ ክፍል

**እንዳይረሱ...**

**እስከ ሴብቴምበር 1 ቀን 2014 ባለው ጊዜ 4 አመት ለሚሆናቸው ልጆች ለ2014-2015 የቅድመ መዋእለ ህጻናት እና ሄድ ስታርት ፕሮግራሞች ምዝገባ በሳመር ወቅት ይቀጥላል። ለተጨማሪ መረጃ፣ 301-230-0676 ደውሉ።**

**የመጀመሪያው የ2ኛ ደረጃ ሳመር ክፍለ ጊዜ ጁን 23 ይጀምራል። ለምዝገባ የመጨረሻው ቀን ሰኞ ጁን 9 ነው። የሁለተኛው ክፍለ ጊዜ ከጁላይ 15 እስከ ኦኦገስት 1 ይካሄዳል። ለሁለተኛው ዙር ለመመዝገብ የመጨረሻው ቀን ጁን 25 ነው።**

**ለኤሌሜንታሪ ፕሮግራሞች፣ ወላጆች በ[የኤሌሜንታሪ የሰመር ት/ቤት ድርጣብያ]** ላይ በሚገኘው የምዝገባ ፎርም (mail-in registration form) መገለገል አለባቸው። **ክፍለጊዜው የሚጀምረው በጁላይ 8 እና የሚያልቀው በኦገስት 1 ነው። ምዝገባው ጁን 20 ይፈፀማል።**